# ማ ባይሆን?

*አሸናፊ አንድዋለም 03-09-18*

ከመሪነት ብቃት ጋር ተያይዞ፣ ባህርይ ወይም ስብእና እንደ ቀዳሚ መመዘኛ ይጠቀሳል። የሰው ባህርይ የሚታወቀው ከዉሎውና ከቃላቱ ነው። የተቀረው ደግሞ ከባድ ፈተና ወይም ወሳኝ ድልና ውድቀት ባጋጠመ ወቅት በሚወስዱ የውሳኔ ምርጫዎች ከሚታይ ብቃትና ጥበብ ይሆናል።

ተወዳጁ የአሜሪካ ፕረዚዳንት አብርሃም ሊንከን፡ "የሰው ትክክለኛ ባህርይ ለማወቅ ስልጣን ላይ አስቀምጠህ ታዘበው" ሲል ተናግሯል። ግን ደግሞ አንዴ ስልጣን ላይ የወጣ ሰው ስብእናው ላይ አንዳች ችግር እንዳለበት ብታውቅ ታዝበህ ምን ታመጣለህ! የአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ነርሲስቲክ ዝንባሌ ከታወቀ ዉሎ አድሯል። ነርሲስት ማለት ራስ-ብርቁ-ሰው-ጤፉ ዓይነት ሰው ነው። ታዲያ አንድ ኤርትራዊ ይህን የኢሳያስ ባህርይ ስለተገለጸለት ብቻ ምን ማድረግ ይቻለዋል? የመንግስቱ አስመሳይና ገዳይ ባህርይ ዘግይቶ የተገለጸላቸው ኢትዮጵያውያን ምን ማድረግ ይችሉ ነበር?

ስለዚህ መጥፎ ጸባይ የተጠናወተው ሰው ካለ ስልጣን ላይ ሳይወጣ የሚቻለውን መሞከር ነው እንጂ ስልጣን ሰጥቶ መታዘብ ለኛ ሁኔታ እሚያዋጣ መስሎ አይታይም። እናም ሊንከንን ይቅርታ ጠይቀን በራሳችን መንገድ እንሄዳለን።

ሰሙኑን የኢህአዴግ ምክር ቤት እንደሚሰብሰብ ስምተናል። የፓርቲውና መንግስት ከፍተኛ ስልጣን ሹመት እሚመነጨው ከዚሁ አካል ነው። እሁድ ዕለት ይጀመራል በተባለውም ስብሰባ የሚኖሩት አጀንዳዎች ይፋ ሆነዋል። ፖለቲካዊ፤ አገራዊና ድርጅታዊ ሁኔታዎችን ገምግሞ ዉሳኔ ለመስጠት፣ በዚያውም ሲጠበቅ የነበረው የአቶ ኃይለማርያምን የስንብት ጥያቄ ተቀብሎ ኢህአዴግን በሊቀመንበርነት፣ መንግስትን በጠቅላይ ሚንስትርነት እሚመራ አንድ ተተኪ ሰው ከራሱ መዞ ያስቀምጣል።

በፓርቲው አሰራር መሰረት የግንባሩ ሊቀመንበር መሆን እሚችለው ከአራቱ እህት ድርጅቶች ሊቀመናብርት ዉስጥ ነው። ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ቦታም እሚመጣው ይህ ሰው ይሆናል ማለት ነው። ሲጀመር፣ ለዚህ ዓይነት ሃላፊነት አንድ ብቁ ሰው ለመምዘዝ የእህት ድርጅቶቹ ሊቀመናብርት ብቻ እጩዎች ሆነው መቅረብ፣ ምርጫው ከጠባብ ሳጥን እንዲሆን ያደርገዋል። ሁለተኛ ብቃት ያላቸው የአጋር ክልሎች ፖለቲከኞች በእጩነት እንዳይታዩ የሚያደርግ አግላይ አሰራር ነው። እሚጎዱት ክልሎቹ ብቻ ሳይሆኑ አገሪቷም ነው። ኢህአዴግ ይህንን አሰራር በፍጥነት ማስተካከል አለበት።

ለአሁኑ፣ አሁን በእጩነት የሚቀርቡትን አራት መሪዎችን የህወሓቱ ዶ/ር ደብረጽዮንን፣ የደህዴኑ አቶ ሺፈራውን፣ የኦህዴዱ ዶ/ር ዓቢይንና የብአዴኑ አቶ ደመቀን እንደሆኑ ግልጽ ነው። ሌላ ምርጫ ቢኖረኝ ከአራቱ እጩዎች እምመርጠው አይኖርም። የግድ ከአንዳቸው ላይ መውደቅ ካለብኝ ግን ከከፋው እጩ ዘንድ እንዳልወድቅ "ማ ባይሆን" የሚል ሃሳቤን ላካፍል። ዋና መመዘኛዬም ባህርይ ወይም ስብእና፣ በፈረንጆቹ character እሚባለው ይሆናል። ቀጥሎ የማረጋጋትና የመምራት፣ ኢትዮጵያውያንን የማስተባበርና የአገር ህልውናና ጥቅም የማስጠበቅ ፖለቲካዊ ቁመና፣ ልማትና ህዳሴ የማስቀጠል ብቃት እያልኩ እሄዳለሁ። መመዘኛዎቹ ፋይዳቸው ካንዱ አንዱ ቢለያዩም በክዋኔያቸው እሚደጋገፉም ናቸው። ለምሳሌ ብቁ ስብእና የሌለው ሰው ሌሎቹ ላይም ደካማ እንደሚሆን ይገመታል። ነገር ግን ብቁ ስብእና ለመሪነት የግድ ነው። ካሉት የተሻለ ለማለት እንጂ ሙሉ-በኩለሄ አይገኝም፣ አንጥበቅም።

ዶ/ር አቢይ አህመድ እስከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለዚህ ኃላፊነት የተሻሉ ሰው ናቸው ብዬ ሳስብ ነበር። ብዙ ክርክሮች ላይም የኢህአዴግ አመራሮች ለኝህ ሰው መንገዱን ሊያመቻቹላቸው ይገባል ስል ተከራክሬ አውቃለሁ። በዚህ አቋሜ ምክንያት የተቀራረበኝ አንድ ሰው እጅግ መሳጭ ቁም ነገር አዘል ንግግሮቻቸውን እንድመለከት ጋብዞኝ በተለይም በዓለማዊ እና በጂኦፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን የጠለቀ እውቀት ለመገንዘብ ጥሩ ምሳሌ ነው ያለውን ይህን ቪድዮ እንድመለከት አጥብቆ ይጋብዘኛል። "የዶ/ር አቢይን የእንግሊዝኛ ችሎታም እግረ መንገድህን ታደንቃለህ" ሲል አከለልኝ። እኔም ትንሽ ፋታ ወስጄ አየሁት።

ባየሁት ነገር ክው ነው ያልኩት።

መጀመርያ ጥያቄዎቹ ለብቻቸው በሌላ የሴት ድምጽ ተነበው እዛው እንደተደረገ በማስመሰል እንዲካተቱ የተደረጉ ናቸው። የጥያቄዎቹ ይዘትም ለሳቸው መልስ አሰጣጥ እንዲመቹ የተመረጡ ናቸው። ዓለም አቀፍ ጉዳዮች፣ አህጉራዊ ጉዳዮች፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የዓለም ሃብት በጥቂት ሰዎች እጅ ሥለመውደቁ ወዘተ በምን መመዘኛ ለኦህዴድ ጽ/ቤት ኃላፊ ሊቀርቡ የሚገቡ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ተደርገው እንደተወሰዱ ግራ ያጋባል። "እርስዎ ፍቅርና ጥልቅ ስሜት ለአንዲት አገር መረጋጋት ወሳኝ ነው የሚል ጠንካራ እምነት አለዎትና እስቲ እዚህ ያለዎትን አመለካከት ያጋሩን" ይላል አንዱ ጥያቄ። ሌላኛው ደግሞ "በዓለም ላይ ያለው መከራና የኑሮ መራራቅ በተመለከተ ያለዎትን ሃሳብ ያካፍሉን ይላል" ሌላው ጥያቄ። ኦሮሚያ በህውከት እየተናጠችና እሳት ላይ እየተጣደች ባለችበት ወቅት ለአንድ ከፍተኛ የክልሉ አመራር መቅረብ ያለባቸው ጥያቄዎች እነዚህ ናቸውን? እየየም ሲደላ ነው!

ዶ/ር አቢይ ከካሜራው በቀር ማንም ሳይኖር አጠገባቸው ቁጭ ብሎ እሚጠይቃቸው ጋዜጠኛ ያለ ያህል፣ ከቴሌፕሮምፕተር እያነበቡ እንደሚመልሱ ግልጽ ሆኖ ሳለ ልክ በቃላቸው እንደሚመልሱ ለማስመሰል የሚረዱ የመስሏቸውን ያልተሳኩ ቅላጼዎች በመጠቀም፣ በቀጥታ ከቴለፕሮምፕተር እያነበቡ እያለ አቀማመጣቸው የቃለመጠይቅ እንዲመስል ሌላ ካሜራ በጎንዮሽ አንግል እንዲያነሳቸው በማድረግ፣ ወዘተ ወጥነት የሌለውና ጥያቄዎቹን እንኳን በአጥጋቢ መንገድ ለመመለስ የማይመጥን መነባነባዊ መልስ ሲሰጡ ይታያል። ለምን ይህ ሁሉ የታይታ ድራማ መስራት አስፈለጋቸው?

“ለጠቅላይ ሚኒስትርነት ከቋንቋ ጀምሮ እስከ አጀንዳዎቹ ማወቅ ድረስ እሚዘልቅ እማያሳፍር ብቃት አለኝ” የሚል ቀሽም ማሻሻጫ መሆኑ የገባኝ ቆይቶ ነው። አንድ ሰው ወደ መሪነት ለመምጣት ራስ-ተኮር ማቆናኛ ለማበጀት ይህን ያህል ሲንቀሳቀስ አንድምታው ምንድን ነው? እዚህ በጣም በተናጠቅ ዓለምና ጂኦፖለቲካዊ ቀጠና ሆነን የዚህ ዓይነት ራስን በማቆንጀት (self-romanticizing) ዘመቻ ላይ የተጠመደ ሰው የራስ መተማመን የሌለው ነውና ችላ እሚባል ችግር አይሆንም።

እኚህ ፖለቲከኛ ከሶስት ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ድርጅት የቦርድ አመራር በነበሩበት ጊዜ ሰራተኞቹን ሰብስበው አወያይተው ነበር። እና ያኔ ስብሰባው ላይ የነበሩ ጋዜጠኞች የወደፊት ህልማቸው ምን እንደሆነ ይጠይቋቸዋል። ዶ/ር አቢይም ሳያለባብሱ እቅጩን ተነገሩ፣ ፊት ለፊት እና በመድረክ፤ “ዕቅዴ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆን ነው!” ያኔ ሲናገሩት የሩቅ ዘመን ዕቅድ መስሎን ያን ያህል ትኩረት አልሰጠነውም ነበር። እሳቸው ግን በዓለም ላይ ያሉት ምርጥ አባባሎቹን ሲሰበስቡ፣ ጥቅሶችን ሲያድኑ፣ እና ለዚህ የስልጣን ጉዞ እሚያገለግላቸውን መስመር ሲያበጃጁ ከራርመው ይኸው ዛሬ ደጃፉን እያንኳኩ ነው።

ጠቅላይ ሚንስትር እሚኮነው ግን እንዴት ነው?

እንደገና ወደ ቃለ መጠይቋ ልውሰዳቹህ። እኔ ቅር ያሰኘኝ “እንዴት አንድ ሰው ራሱን በዚህ መልክ ተፈላጊ ለማድረግ የማቆናኛ ድራማ ይሰራል፤ ያውም ቅሽም ያለ” በሚል ነበር። ለካ ነገሩ የባሰ ነገር አለው። ጭራሽ ዶ/ር አቢይ እንደራሳቸው ሃሳብ እሚያነበንቡት ከሊሎች ሰዎች ጽሁፎችና ንግግሮች ቃል በቃል እንዳለ የተኮረጀ ነው። ዶ/ር አቢይ የተናገሯቸው ከብዙ ሰዎች ቃለመጠይቆች የተወሰዱ ነበሩና ነው። ይህን አስገራሚ ቅሌት ቀጥሎ ካሉት ቪድዮዎች ትመለከታላቹህ። ከየት ከየት እንደተወሰዱ ብሩክ ሚቸል የተባለ ብሎገር በመልክ በመልክ ፈርጆ አስቀምጦታል። አብዛኞቹ የተወሰዱት ግን ከኪሲንጀር ቃለመጠይቅ ነው። በተማሪ ቤት ከትምህርት የሚያባርር ወንጀል እንደሆነ ይታወቃል። በዶ/ር አቢይ ደረጃ ግን የስብእና ጥያቄ ነው እሚያስነሳባቸው።

ሰው እንዴት የራሱ ያልሆነን ሃሳብ እንደራሱ አድርጎ ያቀርባል? በተለይም ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር ላይ ያለ ሰው፣ በተለይም በተለይም የጠቅላይ ሚንስትርነት ኃላፊነት ለመረከብ እሚያልም ሰው?

ዶ/ር አቢይም ሆኑ ክቡር አቶ ለማ መገርሳ ብቃታቸውን ሊያሳዩበት እሚችሉ በቂ ስልጣንና መድረክ ነበራቸው። ኦሮሚያ የተረጋጋች ክልል አልሆነችም። ብቃታቸውም እሚለካው ኦሮሚያ ዉስጥ በሚሰሩት ስራና ኦህዴድ ላይ በሚያሳዩት አመራር ነው። ያኔ እነዚህ ሰዎች በአገር ደረጃም ብዙ ማሻሻል ይችላሉ እሚል ስሜት ከዳር እስከዳር ይስተጋባል። ኦሮሚያ እዚህና እዛ እሳትና ውጥረት እየለበለባት፣ የሰውና የንብረት ደህንነት የአደጋ ደመና እያንዣበበት ባለበት ወቅት የመፍትሄ አመራር ያልሰጠ ሰው ተጨማሪ ኃላፊነት ቢፈልግ ኦሮሚያ ዉስጥ ያለውን ቀውስ በአገር ደረጃ እንዲሰፋ የመፈለግ ያህል ነው።

የኢህአዴግ ም/ቤት አባላት ለራሳቸውና ለፓርቲያቸው የፖለቲካ ህይወትም ሲሉ በውናቸው ዶ/ር አቢይን ጠቅላይ ሚኒስትር አድርገው አይመርጡም ብለን ተስፋ እናድርግ። ግን ዶ/ር አቢይ አሁን ያሉብትም ቦታ ፈጽሞ የሚገባቸው አይደለም። ኦህዴድ ትልቅ ድርጅት ነው። ኦሮሚያ ከብዙ የዓለም አገሮች የምትሰፋና ውስብስብ ችግሮች ያሉባት ክልል ናት። ኦህዴድንና ኦሮሚያን መምራት፣ ኢህአዴግንና ኢትዮጵያን ከመምራት ጋር የሚቀራረብ ትልቅ ኃላፊነት ነው። ታዲያ ዶ/ር አቢይ እዚህ አሁን ያሉበት ላይስ ቢሆን እንዴት ደረሱ? እነ አለማዮህ ቱምሳን የመሳሰሉ ትንታግ ታጋዮች ያልበረከቱባት ኦሮሚያ እሚመጥኗት መሪዎች ለመውለድ ገና ብዙ ምጥ እንደሚጠብቃት ከወዲሁ ይታያል።

-//-